# ትግላችን ዜና

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

Prepared by the Ethiopian Students Union
in Europe

P.O.Box 3198, 10364 Stockholm 3 SWEDEN



ለዘማቾች መታሰቢያ የተዘጋጀ ልዩ እትም /sept.1976/መስከረም 1969

1 ሙሉጌታ አያሌው
2 ደረጀ ለመገሀ
3 ተገኜ ከፋር
4 አሰፋው አለነ
5 ገብረ ቀሃገስ ገሠሠ
6 ገርማ ቶሎ
7 ዘውዴ ተካ
8 አበር አለቃ ወንድዬፍራው አለነ
9 ወይንአሸት ጥላሁን
10 መርሻሎ ለማ
11 ያለም ዘውዴ ገርማ
12 ንዝው ለበታ
13 ዳምጠው ጌቢሻ
14 ዘርይሁን አደራ
15 ሰጬ አለም ጉተማ
16 ያሬድ ሙሉጌታ
17 ባባሁን አበበ
18 አሌ ሃበገ
19 በተረወርቅ ከበደ
20 የወብናር ተስፋሉ
21 ተሾመ ወቴፓ
22 ቢዘን ወለደ ጊዮርጊስ
23 መኮንን አሰማማው
24 አበራ ባዩ
25 አሸቱ ወለደ ጊዮርጊስ
26 ፋንታ ረጋሳ
27 አለማየሁ ኝቱኛ
28 አራጋው ሜሬንኝ
29 ባባ ጌሳ
30 ጥላሁን ሃገኮ
31 ተሾመ ይለማ
32 ፈቃደ እንግሊዙ
33 ታዬ ገብረ ህይወት
34 ተርፈ አለሙ
35 ሸጠሙ ታዬ
36 በበረተ ዮከሬ
37 ቃደስ ቃሙ
38 ሚካኤል ፓርፎ
39 ክቶማ ከበደ
40 ተከለ ንሻው
41 ሻገበስ ሃይለ ማሪያም ደምሴ
42 ከፍሌ ደበታ
43 ወይዘሮ አለማዘ
44 ጌታቸው ለገሰ
45 ቀበነሳ ገሻ
46 መኩሪያ አማን አገራው
47 በር ሃኑ ሰሜ
48 ገነት ሰዛ
49 መርቆሬ ዎስ ወዳጅ
50 ተስፋ ሚካኤል ጥላሁን
51 በር ሃኔ ተኪዬ
52 አበበ አበቤ
53 በለጠ በሳይነህ
54 ሃይለ ማሪያም ነገና
55 ፒቴ ኦፊሰር ሙሉጌታ አሰፋው
56 አበባል ከፋር ሁሴን
57 ወታደር ፓርጬ ዳፋ
58 አጬን አየሁ ደበለ
59 አሰራት ይሰማው ጌዲ
60 ገርማ ተሻለ
61 ታሬ ግርበ
62 ስስማን አሌ
63 አለምአየሁ አይማሩ
64 ዲሬባ ደበሳ
65 ንጋሁን ማሰረሻ
66 በርናኔ አበበ

67 ቶማስ ለደቀ
68 መኮንን ሺፈራው
69 ገነት በርሄ
70 አሰማዝ በላይ
71 ሳሙኤል በዳሳ
72 ተኪኤ በርሄ
73 ነጋ አጆም የለሁ
74 ታደሰ ገብረ መስቀል
75 ሙሬ ነሁ መሰፍን
76 አሰፋ ይለማ
77 አለሙ መሳኩ
78 ቁሃገስ ሙሳት
79 በረከ ገንኡ
80 ፍሰሃ ገብረ ወዱደገ
81 ገርማ ተፈሪ
82 አሰፋሽ ተሰፋ ማሪያም
83 ሄሩት ፊሊጶስ
84 ቢኒያም ሰዑል በገዱ
85 ገርማይ ሃዱጉ
86 ሃይለ ማሪያም ገብረ ፃዲቅ
87 በሳይ ወንደሙ
88 ተከተለ ሃይለ ማሪያም
89 ቁሃገስ አይማሉ
90 በሰቀን ጌታቸው
91 ካሳዬ መኩዬ
92 ወንዲሁራድ በቀለ
93 አለባቸው ደሳለኝ
94 ገርማ ቃገስ
95 ዘውዱ አጋ
96 አሰፋ አበራ ሃ
97 መርጊያሽ በርሄ
98 በሰቆን ወንዳፍራሽ
99 ጌጤቀን በቀለ
100 የንጉሡነሽ ንጋቱ
101 መሰከሙ ገበት
102 ረጋሳ ደሬሳ
103 ደምሴ ከበደ
104 መሰረት ሺፈራው
105 ይሽነቁ አሰፋ
106 ገዛሽኝ ሃይሉ
107 ረታ ገዛሽኝ
108 መኩዱ አህመዱ
109 ተሾመ ይርሳው
110 በቀለ መኩሪያ
111 ጨነ ፍቅሬ
112 አፍወርቅ አለሙ
113 በሳይ ይመር
114 አሰፋው ወንደም አገኘሁ
115 ፍቅሬ ሃይሉ ::



ከሁለት ዓመታት በፊት በታወጀው የእድገት በህብረት ዘመቻ ለማ ኪኝነት ከሰፊው ሕዝብ ጋር ተዋሃዱ የሚለውን መሪከር ሥራ ላይ ለማ ዋል በገጠርና በከተማ ከተሰማሩት ወጣቶች ምሁራን ስማቸው ከዚህ በ ላይ የተዘረዘረው ዘማቾች ጓደኞችን ሰፊው ሕዝብ እንዲነቃ፣እንዲደራጁ ና እንዲታጠቅ በሚደረገው ከፍተኛ ትግል ውስጥ ህይወታቸውን ለአብዮ ት ሰጥተዋል::

ከልዩ ልዩ አደጋና ከፀረ አብዮት ሃይሎች ጋር በመጋፈጥ ከሰፊ ው ጭቁን ሕዝብ ጎን በመሰለፍ፣ለዚሁ አብዮታዊ ተግባር ህይወታቸውን የሰዉ ናቸው::

ከዚህም ተነስተን ከትግላቸውና ከመስዋእትነታቸው የሚገኘውን ት ምህርት መቅሰም ተገቢ ተግባራችን ነው::

በነፃነታችን ጉዳና ላይ ሌሎች ሰማእታት ደጋግመው ለሃገራቸው ወድቀዋል ወደፊትም የሚወድቁ ይኖራሉ::

እነዚህ ዘማቾች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና ደህንነት ሕይወታቸ ውን መስዋእት ካደረጉት ወንድሞቹና እህቶቹ ጋር አንድ ሆነዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የነዚህን ሰማእታት ደም በርግጥ ይበቀልላቸዋል:: የኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል ታሪክም ዘላለም ሲያስታውሳቸው ይኖራል::

ለነዚህ ወጣት ወገኖቻችንም ሆነ በጠቅላላው ለአገራቸን ነፃነት ሲታገሉ ለወደቁ ኢትዮጵያዊያን ልንሰጠው የምንችለው ከፍተኛው ክብር ትተውልን የሄዱትን አረያነት በመከተል ትግላቸውን ከግቡ ለማድረስ መጣጣር መሆኑ ይገባል::

ምንጊዜም ከልባችን የማይጠፉት ወጣት ወገኖቻችን በበገቱ አለ ፉም::በትግላቸውና በመሰዋእትነታቸው አርአያነት ትግላቸውን የም ቀጥለው የኢትዮጵያ ወጣቶች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተዋህደን ገፈኞች ንና አድርባዮችን ደምሰሰን አዲሲቷን ኢትዮጵያ በመሠረት ለፈሰሰው ደማቸው ግምት የማይገኝለት ዋጋ እንሰጠዋለን::

ትግላችን ዜና

## ዘመቻውና የተማሪዎች ሚና

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ከብዙ ዓመታት ጀምሮ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት ጠር የሆኑትን ኢምፔሪያሊዝምንና ፊውዳሊዝምን ሲታገል የቆየ ማህበር ነው:: ዛሬም አብዮታዊው እንቅስቃሴ ተፋፍሞ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ሰዓት የትግሉን ፈለግ በመከተል ያውሮፓ ማህበር ከሰፊው ህዝብ ጎን ሆኖ ይፋለማል::

በ16ኛ ጉባዔ ማህበራችን ያሳለፈው ውሳኔ ለዚሁ የማያዳግም ማረጋገጫ ነው::

ስለሆነም ዛሬም እንደትላንት የአብዮታውያን አጋር ከመሆንም በላይ አብዮታውያን ለሚያደርጉት ትግል የማያቋርጥ ድጋፍ መሆኑን እያረጋገጠ በመሄድ ላይ ነው::

ከዚህ መሠረታዊ ሚና በመነሣት በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በአገራችን በኢትዮጵያ ከሰፊው ሠርቶ አደር ጎን ተሰልፈው ከፍተኛ ተጋድሎ ላደረጉት ዘማቾች አብዮታዊ ድጋፉን ሰጥቷል፣ ለወደፊትም ይሰጣል::

ማህበራችን ይህንን ድጋፉን ሲሰጥ በጊዜ በመሠረቱ የአብዮታዊ ወጣቶች ተግባር ከሰፊው ህዝብ መማርና ከሰፊው ህዝብ መማርና መልሶም ማስተማር ነው ከሚለው እምነት ተነስቶ ነው:: ይህንን ጥቅ ሃው ተግባር እስኪፈጸም ድረስ ደግሞ ማህበራችን ተባባሪነትን በሥራ መተርጐሙ ለወደፊትም ይቀጥላል::

## የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ዘመቻው

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ "ተማሪና ምሁር ከሠራተኛውና ከገበሬው ተዋሃዱ፣ ከነርሱም ተማሩ፣ መልሳችሁም አስተምሩአቸው፣ አብረህ በመሰለፍ አዲሲቷን ኢትዮጵያ መሥርት" ከሚለው አብዮታዊ መፈክር ሥር ተሰልፈው ላያሌ ዓመታት ከፍተኛ ትግል አድርገዋል:: በዚህ ትግላቸው ብዙ ስቃይና ችግር ደርሶባቸዋል::

ይሁንና ስቃይና ችግር እርምጃቸውን ሳይገታው አብዮታዊ ትግል በማካሄድ ከፍተኛ ውጤት ማግኘታቸው አልቀረም::

ስለሆነም የኢትዮጵያ ተማሪዎች ያደረጉት ከፍተኛ ትግል ከቀሪት ጭቁን የህብረተሰብ ክፍሎች ትግል ጋር ተደምሮ በየካቲት 1966 የፈነዳውን ሰፊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ወልዶዋል::

የየካቲት እንቅስቃሴ በፈነዳበት ሰዓት ሃቀኛ ተራማጆች የአላማውን ትክክለኛነትና የትግላቸውን ፍሬአማነት የተረዱትን ያህል፣ ከገቀና ጭው ጉድለቶች ደግሞ ለዓላማቸው አሁንም በይበልጥ መታገል እንዳለባቸው ሳይገነዘቡ አልቀሩም::

በየካቲት እንቅስቃሴም በተራማጅ ወጣት ዘንድ ሃይለኛ የትግል ስሜትና ብርታት ይታይ የነበረው ከፍ ብለን እንዳልነው ሰፊው ተማሪ ለብዙ ዓመታት /በተለይ ከ1962 ወዲህ/ በሰፊው ህዝብ ዘንድ ባደረገው ቅስቀሳ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠቃሚ



ውጤት በማግኘቱ ነበር:: ማለትም ሰፊው ተማሪ ለብዙ ዓመታት የተከተለው መሪ ቃል ትክክልና ጠቃሚ መሆኑን ስለተረዳው ነበር::

በሌላ በኩል የየካቲትን እንቅስቃሴ ውስንነት የተመለከቱት ሃቀኛ ተራማጅ ወጣት ይህ እንቅስቃሴ በይበልጥ ሥር እየሰደደ እንዲሄድና ጉድለቶቹ እንዲወገዱ ምኞት ስላደረበት፣ ከሰፊው ህዝብ ተዋህዶ ቅስቀሳውን በይበልጥ ለማካሄድ ያደረበት ጉጉት ያንኑ ያህል ነበር:: በየካቲት 66 ገደማ የተማሪው የትግል ዘዴ ለቀ ሊታይ የቻለው ከዚሁ የተነሳ ነው::

እንግዲህ ይህ ሁኔታ በነበረበት ሰዓት ተማሪው ባንድ በኩል ባገኘው ውጤቶች ተደስቶ በሌላ በኩል ትግሉን ለመቀጠል ከፍተኛ ምኞት አድርቦት በነበረበት ሰዓት በተለይ በአገር ቤት የሚገኙ ወጣቶች አብዮታዊ ሚና ከበፊቱ አስር ጊዜ በልጦ ይታይ ነበር::

ይህንና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በ"ደጉ" ጊዜ ዘመቻውን አፋፍቶ የተመጠው የተማሪው አድሃሪ ክንፍ ይህንን ከፍተኛ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ባየበት ወቅት፣ ተራማጁ የተደሰተውን ያህል እሱ ወደናገጡ አልቀረም::ለመጀመሪያ ጊዜም በፖለቲካ መስክ ውስጥ በግልጽ ዘመቱን ማሰማት የተገደደው በዚሁ በአብዮታዊ ወቅት ነው::

በሌላ አነጋገር የሰፊው ህዝብ ትግል እያየለ ሲሄድ በተራማጅ ተማሪዎችና በአድሃሪ ተማሪዎች መሀል ያለው ልዩነት ግልጽ እየሆነ ለመጣ ችሏል:: በዚሁ መጠን በአገራችን በነበረው ትግል ውስጥ እነዚህ ሁለት ክፍሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ የሚሄዱ ተቃራኒ ሚና ሲጫወቱ ታይቷል::

ከፍ ብለን እንዳልነው የተማሪው ተራማጅ ክንፍ ትግሉን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀጠል ከመቼውም ይበልጥ ዝግጁ በነበረበት ሰዓት የደመኛውን የሃይለ ስላሴን መንግሥት የተካው ደርግ፣ የተማሪው ፍላጎት ይሟላ ዘንድ በቂ የትግል መስክ አላከፈተም ነበር:: እንዲያውም ፈጽሞ ፀረ ዲሞክራሲ አዋጅ በማውጣት ብዙውን ተማሪ አስቆጥቷል:: በነገራችን ላይ በዛን ሰዓት "ለጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት" ደጋፊዎች ለዚህም ዓላማቸው ደርጉን ፋሽስት በማለት ለተነሳሱ ሃይሎች በወጣቱ ዘንድ ድጋፍ የተገኘው በዚሁ ሰበብ ነው ለማለት ይቻላል::

የሆነው ሆኖ፣ ይህ የተማሪው ተራማጅ ክንፍ ባብዛኛው በከፊል ደርጉን ፋሽስት በሉ "ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት" ይመረጥ ወደሚለቱ ቢያዘነብልም ቅሉ፣ አብዛኛው ለትግል ከፍተኛ ጉጉት ይታይበት ነበር:: "ህብረተሰባዊነት" በታወጀበት ጊዜና ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የእድገት በኅብረትና የሥራ ዘመቻን ባወጀበት ጊዜ ሰፊው ተማሪ በደስታና በሆታ የተቀበለውም ለዚሁ ነው::

በዚህን ጊዜ ግልጽ የሆነ አድሃሪ ሚና መጫወት የጀመረው ክንፍና ምናልባትም በገጠር ሄዶ የከተማውን ምቾትና መንደላቀቅን ማጣት የፈራው ክፍል፣ እንዲህም ደግሞ በደርጉ ፀረ ዲሞክራሲነት በደርጉ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ያደረበት ቡድን በክሳሽ የንዑስ ከበርቴ ሰፈር ጋዜጦች በመመራት ዘመቻውን ባንድነት ተቃውሞአል::

የመጀመሪያዎቹ የሚሰጡት ምክንያት ከፀረ አብዮት ወይንም ከግል ምኞት አንፃር ሊሆን ሁለተኞቹ " ጊዜአዊ ህዝባዊ መንግሥት ካልተቋቋመ አንገዛምትም "፣ " ደርጉ የሚያዘምተን ከከተማ ሊበታትነን ነው " ወይም ደግሞ " ፋሽዝምን በገጠር ለማጠናከር ነው " ወዘተ... የሚሉ ምክንያቶች በመስጠት ነበር:: ከዚህም ተነስተው በዘመቻው ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት ካደረበት ተማሪ ዘንዱ ከፍተኛ ቅስቀሳ በማድረግና ሲያስፈልገንም ማስፈራሪያ በመስጠት ከዘመቻው ለማስቀረት ብዙ ሙከራ አድርገዋል::

እዚህ ላይ በዘመቻው አለመሳተፍ የመረጠው ቡድን የሚሰጣቸውን ምክንያቶች መመርመሩ ይጠቅማል::

ከፀረ አብዮት አንፃር ዘመቻውን የተቃወሙት " ሸሙጥ " የምትባለው ጋዜጣ እንዳሉት " ተማሪና ትፈሳ ደር የሌለው ገበሬ ሲገናኙ ደግ አይደለም " ከሚሉ የአድሃሪያኖች እምነት ተነስተው ነውና እንመለስበትም:: ይልቁኑ በተራማጅ መሰል ምክንያቶቹ ዘመቻውን አተቃወሙ ላይ እናተኩር::

በመጀመሪያ ከቀረቡት ምክንያቶች አንደኛው " ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት ካልተቋቋመ አንገዛምትም " የሚለው ነው::

ከሁሉ አስቀድሞ ይህ ጥያቄ መታየት ያለበት ራሱ "ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት ይቋቋም" የሚለው ጥያቄ ትክክለኛነት ወይም ስህተኛነት አንፃር ነው:: ይሁንና የዚህን ጥያቄ ከሳሽነትና ቀለበሽነት መጽሔቶቻችን በበቂ አሳይተውታል፣ እዚህ ላይ ማተቱ ትርፍ ይመስለናል::

በሁለተኛ ደረጃ ዘመቻውን ለመቃወም የቀረበው ምክንያት በቂ አለመሆኑን ለመረዳት የጥያቄውን አቀራረብ ማየት ይበቃል::

- በዘመቻው በመሳተፍ በሰፊው ገበሬና በሠራተኛው ዘንድ ማድረግ የሚቻለውን ቅስቀሳ በመገንዘብ፣
- ምን ያህል ሰፊውን ገበሬ ማደራጀት እንደሚቻል በመረዳት፣
- ከዚህም አለፍ ደግሞ በተለይ መንግሥት የማቋቋሙን ሙሉ ተግባር የሰፊውን ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ በትግል መሳተፍ መጠየቅን በማወቅ፣

ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት ካልተቋቋመ አንገዛምትም ማለት በብዙ ትግል የሚገኝ ድል ያለትግል ካልተገኘ አንታገልም እንደማለት ነው::

ይህ ደግሞ ድሉ እንዳይገኝ የሚፈልጉትን ፀረ ህዝቦች እንጂ ድሉ እንዲገኝ የሚፈልጉትን የህዝብ ወገኖች አይጠቅምም:: ስለዚህም በእውነት በቂ ምክንያት አልነበረም::

ሌላው የቀረበው ምክንያት አይነት ደርጉ ተማሪውን የሚያዘምተው ፋሺዝምን በገጠር ለማጠናከር ነው ወይም ደግሞ ዘማቾች የደርጉ " ጥቁር ሸሚዞች " /ብላክ ሸርትስ/ ናቸው የሚለው በንኩል ምክንያት ነው:: በእውነቱ ለዘመቻ ደርጉ እርግጥም ፋሽዝምን ለማስፋፋት የተነሳ ሃይል ቢሆን እንኳ፣ ወደ ተማሪውን ፋሺስት ያደርገዋል ብለን እስከማሰብ /ይህ ደግሞ ተማሪዉን መናቅ ብቻ ሳይሆን በተማሪው መሳለቅም ጭምር ነው/ ወደ ያሜሪካን ኢንሳይክሎፔዲያ እንደሚለው ቦልሸዝምን ሙሰለ" ፋሽዝም" /!/ ያስፋፋል ብለን እስከሚሰፋን ደረስ፣ ይህ



ምክንያት ቦታ አይኖረውም::

እንዲያውም እንደዚህ አይነቱ ሰበብ ቀን ከሆኑ ነገር ግን ከትግሉ ተሸማቾች መነጨ መሆኑ ያጠራጥራል::

ሦስተኛው ምክንያት " ደርጉ የሚያዘምተን የተማሪውን ሃይል ከከተማ ሊበታትነን ነው" የሚለው ነው:: ምናልባት ከቀረቡት ልዩ ልዩ ምክንያቶች ይበልጥ ሊታሰበበት የሚገባው ይኸኛው ነው ለማለት ይቻላል:: ምክንያቱም ተማሪው በይበልጥ ትግሉ ውስጥ የሚጠቅመው እዚው በከተማ እንደተሰበሰበ ቢቆይ ነው ወይስ በገጠር ሄዶ ሰፊውን ገበሬ በማንቃት ነው የሚለውን ጥያቄ ያስጠይቃል:: ይህ ደግሞ ለትግሉ ወሳኝ የሚቆረቆሩ ተራማጆች የሚያቀርቡት ጥያቄ ነው:: ዘመቻውን ለመቃወም ከተዘረዘሩት ምክንያቶች በይበልጥ ሊታይ የሚገባው ይኸኛው ነው ያልነውም ለዚሁ ነው::

ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ መልሶች ተሰጥተዋል:: ባንድ በኩል በዘመቻው መሳተፍ በከተማ የሚገኘውን የተደራጀ የተማሪ ኃይል መበተን መሆኑን በማየት የተወሰነው ምንአልባትም ተማሪው ራሱን ሳያደራጅ በገጠር ከተበተነ ጠቃሚ ሥራ ሊሠራ አይችልም ከሚለው ግምትም በመነሳት በከተማ መቅረትን መረጠ አለ:: በሌላ በኩል፣ በከተማ ተጠራቅሞ ትግሉን በከተማ ብቻ ከመወሰን በአገሪቷ በመላ /ቢቻል በተደራጀ መልክ/ ተበታትኖ በየአቅጣጫው ሰፊ ቅስቀሳ ማድረግ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከሰፊው ገበሬ ጋር ህብረት መፍጠር ይበልጥ ጠቃሚ ነው ብሎ የገመተው ክፍል በዘመቻው መሳተፍን መርጧል::

እንደውነቱ ከሆነ ይህ ጥያቄ በተነሳበት ሰዓት ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት በቂ መሳሪያ አልነበረም:: ይሁንና ዛሬ ወደ ኋላ ተመልሰን መዘመት መረጡት ዘማቾች ያከናወኑትን ተግባር ስናይ በዛን ጊዜም ቢሆን ዘመቻውን መቀበሉ ትክክለኛ እንደነበር እንረዳለን::

የሆነው ሆኖ ይህ ጥያቄ ቁርጠኛ መልስ ያገኘው፣ ዘመቻው ከተጠራ ጥቂት ወራት በኋላ መሬት አዋጅ ሲታወጅ ነው:: ይህ አዋጅ ሲታወጅ የተማሪው በከተማ መቆየት ምንም የማይጠቅምና የተማሪው በገጠር ተሰማርቶ አዋጁን በሥራ መተርጎም ምን ያህል ጠቃሚ አስተዋጽኦ ሊሆን እንደሚችል በግልጽ ታይቷል:: ዛሬም የዘመቻውን ውጤት ወደ ኋላ ተመልሰን በምናይበት ጊዜ የዚሁን ግምት ትክክለኛነት እንረዳለን::

ለማጠቃለል ያህል በየካቲት እንቅስቃሴ ባንድ በኩል ሰፊው ተማሪ በከፍተኛ ደረጃ ሲነሳሳ በሌላ በኩል በንቅናቄው መጐልመስ የተደናገጡ አድሃሪ ተማሪዎች በግልጽ መታየት ይጀምራሉ:: ከዚያም ዘመቻው በተጠራበት ጊዜ አድሃሪ ተማሪዎች ከፀረ አብዮት ግምት ዘመቻውን ሲቃወሙ፣ የተረፉት ደግሞ ከሌሎ በንኩል ምክንያት በማቅረብ ከፊሎም እውነትም አብዮቱን የጠቀመ መስሎት ላለመዝመት ወሰኑ:: ሰፊው ተማሪ ግን በተለይ ከአዲስ አበባ ውጭ ያለው ተማሪ ዘመቻውን ተቀብሎ ሊዘምት ችሏል::

ትክክለናው እቃ በዘመቻው በመጠቀም ከሰፊው ህዝብ በይበለጥ ለመቀ ሃዱ መቀከሩ እንደነበር ዛሬ የማይጠረጠር ሃቅ ነው::

የሆነው ሆኖ የዘመቱትም ዘመቶች አለመዘመትን የመረጡት በሰቆ ሰቆ ዘዴ በከተማ ለመቅየት ቀከሩ ያልቻሉትም ሳይወዱ በግድ በደርጉ ማስጠንቀቂያዎች ተደናገጠው ወደ ዘመቻው ሄዱ:: በማህል የመሬት አዋጅ ታወጀ::

በታሳቅ\ የትግል መገፈስ ተገፋፍተው የዘመቱ ተማሪያዎች በተለይ የመሬት አዋጅ ሲታወጅ ተገባራቸው በይበለጥ ሊከበትላቸው ችሏል::በየገጠሩ ገበሬውን ማደራጀትና መሬትን ማከፋፈል ጀመሩ::

ይህንን ትግል ዘማቾች በጀመረበት ሰዓት የገበሬው የንቃት ደረጃ፣ አዋጁን በሥራ ለመተርጎም የነበረው ፍላረትና ቁራጥነት በእውነቱ በቂ አልነበረም:: ከተባበረ ባላባቶን ፈንቅሎ ለመጣል እንደሚቸል ገበሬው በበቂ ተገንዝቦ ነበር ለማለት አይቻልም:: ስለዚህም የዘማቾች የመጀመሪያ ከፍተኛ ሚና፣ ለገበሬው ፍላረት መስጠት፣ ገበሬውን አስተባበሮ ባላባቱ ላይ ማስነሳትና መሬትን ሰሥነ ሥርዓት መከፋፈል ነበር::

ይህንን ተገባራቸውን ለመፈጸም በሚታገሉበት ጊዜ ዘማቾች በዙ እንቅፋት ገጥሞአቸዋል::

በመጀመሪያ ራሱ የዘመቻ መምሪያው በበቂ የተደራጀ አካል አልነበረም:: ዘመቻውን በሥነ ሥርዓት ለማካሄድ ብቁ ሆኖ አልታየም:: በበዙ ቦታዎች የማይናቁ ጉድለቶች አሳይተዋል:: በሌላ በኩል ከደርጉ ቀኝ ክንፍ እንስቶ እስከ ፖሊሱ፣ከመንግሥቱ ቢሮክራሲ እንስቶ እስከሸፈተው ባላባት ድረስ፣ በዘመቻው ላይ ከፍተኛ ሴራ ተጠንስሰዋል:: ዘማቾችም በደርጉ የሚተሳለፋትን አንዳንዱ አዉሃሪ መግለጫዎች ከገጠሩ ፖሊስና ቢሮክራሲ የሚመጣባቸውን ጥቃት፣ እንዲሁም የሸፈተው ባላባት የሚያወርድባቸውን የጥይት ናዳ ለመቋቋም በቂ መከላከያ መሣሪያ ስላልነበራቸው፣ በዚህ አንፃር መምሪያው ብዙ ጉድለት ስለታየበት፣ በበዙ ስፍራዎች ከማህከላቸው ህይወታቸውን ያጡ አሉ::

እነዚህን ችግሮች ዘማቾች የተመለከትዋቸው በሁለት አይነት ነው::

ከፊሉ፣ ማለትም ሳይወዱ የዘመተው አዉሃሪ ተማሪ፣ የከተማ ምቾት ፍናፊቱ፣ እንዲሁም ደገዉ በዘመቻው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ባሰሙት ቀለባሽ ስወር ጋዜጦች የተወናበደው፣ በነዚሁ ችግሮች በማመካኘት፣ ዘመቻውን ትቶ ለመሄድና ሰፊውን ተማሪ በሱ ሥር ለማሰለፍ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: መከራውም በከፊል ተሳክቶለታል:: ሌላው ወገን ይህንን ሁሉ ጥቃት ተቋቁሞ አበቃታዊ ትግሉን ቀጥሏል:: በዚህም አንፃር በትግል ለቀቀት ዘማቾች በከንቱ እሰቃታቸሁ ሊያስገኙላቸው ችለዋል እንላለን::

ምናልባት እነዚህ ቁራጥ ዘማቾች ትግላቸውን በትጋት ባይቀጥሉ ኖሮ ከተቋቋሙት 22.000 ከሚሆኑ የገበሬ ማህበራት ሩበም ባልተቋቋመ ነበር:: ከዛም አልፎ የተሰሩት ት/ቤቶች፣ የህክምና ስፍራዎች፣ የገጸህና ቤቶች፣ ለመሃይማን የተሰጠው ትምህርት የሚናቅ አይደለም:: ለዚህም የሚቀጥሉትን ሰንጠረዦች* ማየቱ ይበቃል::



5. የለቃ ለቃ ሥራ በገጠሮች አገዛዊ መዘርዝር

/ከቀላ ጉደለ/

በ1967 እና በ1968 ዓ.ም ዘማቾች ያደራጁዋቸው የገበሬ ማህበራት በክፍለ ሀገራት

| ተ. ቁ. | በክፍለ ሀገር /በፊደል ቀደም ተከተል | ጠቅላላ የገበሬ ማኅበራት በዛት | ጠቅላላ የአባሎች በዛት | ጠቅላላ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ በዛት | ጠቅላላ የፍርድ ሸንጎ በዛት | ጠቅላላ የጥበቃ ጓድ በዛት | በገበሬ ማህበራት የቤቶች አባላት በዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 1971 | 728227 | 8181 | 6698 | 10200 | 32719 |
| 2 | ሲዳሞ | 1508 | 404861 | 8452 | 4661 | 14271 | 41692 |
| 3 | ሸዋ | 4039 | 1230162 | 22124 | 14374 | 34818 | 49826 |
| 4 | በጌምድር | 1025 | 464291 | 7645 | 3154 | 9061 | 4231 |
| 5 | ባሌ | 941 | 128644 | 5968 | 2531 | 10018 | 7638 |
| 6 | ትግሬ | 1329 | 324788 | 6176 | 4241 | 5275 | 67700 |
| 7 | አሩሲ | 979 | 236507 | 5552 | 4323 | 20654 | 29030 |
| 8 | ኢሉባቦር | 816 | 118432 | 1935 | 887 | 3840 | 18 |
| 9 | ከፋ | 1504 | 345719 | 5520 | 3857 | 4030 | 7348 |
| 10 | ወለጋ | 1943 | 404529 | 9774 | 8059 | 34347 | 80084 |
| 11 | ወሎ | 1240 | 360850 | 7049 | 3441 | 1138 | 42906 |
| 12 | ገሙጎፋ | 458 | 163469 | 3147 | 1536 | 120 | 19361 |
| 13 | ጎጃም | 1741 | 527333 | 9187 | 5858 | 7421 | 74427 |
| | ጠ/ድምር | 19314 | 5537812 | 100710 | 63620 | 55193 | 456980 |

* ሰንጠረዦቹ የተወሰዱት ከ1967ና 1968 የዘመቻ ክበብን አጠቃላይ ዘገባ — ጥራዝ 1 — ገጽ 171 እስከ 175

በ1967 እና በ1968 ዓ.ም በዘማቾች አማካይነት በተከፈቱ የመሠረተ ትምህርት የተከታተሉ የሕዝብ ብዛት በክፍለ ሀገር

| ተ.ቁ. | ክፍለ ሀገር /በፊደል ቅደም ተከተል/ | ለመማር የደረሰ ገጠ መቀሳሳ ብዛት | በሰቆ ለቆ ቃክ ገያት ከመከከሰ ያቋረጡ ብዛት | የጎለመሱን የመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ ብዛት | ሁሉም አካባቢውን በጠናከረ ጊዜ በትምህርት ላይ የነበሩ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 88108 | 20958 | 12663 | 45332 |
| 2 | ሲዳሞ | 82223 | 52054 | 15225 | 37588 |
| 3 | ሸዋ | 247557 | 62066 | 45551 | 41117 |
| 4 | በጌምድር | 10864 | 3093 | 7282 | 489 |
| 5 | ባሌ | 19843 | 2976 | 1075 | 3342 |
| 6 | ትግራይ | 61015 | 7347 | 24583 | 2650 |
| 7 | አርሲ | 54602 | 12436 | 17732 | 24434 |
| 8 | ኢሉባቦር | 23433 | – | – | – |
| 9 | ከፋ | 50667 | – | 4000 | 21165 |
| 10 | ወለጋ | 46219 | 13775 | 22074 | 8667 |
| 11 | ወሎ | 10592 | 324 | 42 | 266 |
| 12 | ጋሞጎፋ | 27661 | – | – | – |
| 13 | ጎጃም | 33393 | 7908 | 7838 | 17642 |
| | ጠቅላላ ድምር | 756176 | 182937 | 158065 | 202697 |



በ1967 እና በ1968 ዓ.ም ዘማቾች ያከበሩያቸውን የሕዝብ በማስተባበር ከሰቆ ሰቆ ድርጅቶች
ጋር በመተባበር ያከናወኗቸው የእርሻ ፕሮግራሞች በክፍለ ሀገር

| ተ.ቁ. | ክፍለ ሀገር /በፊደል ቅደም ተከተል/ | የጋር እት ከለት ሰርቶ ማኅበራት | የደር እር ቢታ ሠርቶ ማኅበራት | የገበ እር ቢታ ሠርቶ ማኅበራት | የዘና ቸገገ ወደበ ሰርቶ ማኅበራት | ወዘገር ማኅበሩ ቁያ ጉ ድጋፎች | በመቆሳሳው የተተከሉ ሰቆ ያዘና ችገኞች ብዛት | በመጠ የተከተ ለ ከበ ተ ብዛት | አ ጀርበ የተከተ ከበት ብዛት | ገገፈ የተከተ ከበት ብዛት | አባበገ የተከተ ከበት ብዛት | አባገርክ የተከተ ከበት ብዛት | ደበታ የተከተ ከበት ብዛት | ፎበ የተከተ ከበት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | – | – | – | – | – | 49440 | | | | | | | |
| 2 | ሲዳሞ | 54 | 3 | 3 | 14 | – | 2000 | 1500 | 1500 | – | – | – | – | – |
| 3 | ሸዋ | 51 | – | – | 1 | – | 1034344 | – | – | – | 29365 | 3140 | – | – |
| 4 | በጌምድር | 1 | 1 | -- | 1 | – | 49866 | – | – | – | – | – | – | – |
| 5 | ባሌ | 70 | – | – | 1 | – | 10000 | – | – | – | – | 40400 | – | – |
| 6 | ትግራይ | 54 | – | – | 63 | – | 650533 | – | – | – | – | – | 7108 | – |
| 7 | አርሲ | 43 | – | – | 16 | – | 105064 | – | – | – | 500 | 1600 | – | – |
| 8 | ኢሉባቦር | 31 | – | – | – | – | – | – | – | 794 | – | – | – | – |
| 9 | ከፋ | – | – | -- | – | – | 144973 | – | – | – | – | – | – | – |
| 10 | ወለጋ | 260 | 1 | – | – | – | 28000 | – | – | 1039 | 9800 | 20018 | 180000 | – |
| 11 | ወሎ | – | – | – | 8 | – | 9500 | – | – | – | .. | – | – | – |
| 12 | ጋሞጎፋ | 4 | – | – | – | – | 1630 | – | – | – | – | – | – | – |
| 13 | ጎጃም | 47 | – | – | – | – | 257 | – | – | – | 600 | 2000 | 1100 | 3000 |
| | ጠቅላላ ድምር | 615 | 5 | 3 | 104 | – | 2075607 | 1500 | 1500 | 1833 | 40265 | 67158 | 188208 | 3000 |

በ1967 እና በ1968 ዓ.ም ዘማቾች ያከባቢያቸውን ሕዝብ በማስተባበር ከሰፈ ለፈ ድርጅቶች ጋር
በመተባበር ያከናወኗቸው የጤና ፕሮግራሞች በክፍለ ሀገር

| ተ.ቁ. | ክፍለ ሀገር /በፊደል ቅደም ተከተል | ሳንባ/ቢሲጂ/ የተከተበ ሰው ብዛት | ፈንጣጣ የተከተበ ሰው ብዛት | የወባ መርጨ | ዲ.ፒ.ቲ. የተከተበ ሰው ብዛት | የሰለጠኑ የገጠር አዋላጆች ብዛት | የጤና ገለጻ የተደረገለት ሰው ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 39953+ | 51104 | — | — | — | 10100 |
| 2 | ሲዳሞ | 1400 | 82441 | 30900 | — | 44 | 56169 |
| 3 | ሸዋ | 46446 | 464556+ | — | 4166 | 431 | 206512 |
| 4 | በጌምድር | 19937 | 21977 | — | — | 10 | 28200 |
| 5 | ባሌ | 10567 | 11137 | — | — | — | 7300 |
| 6 | ትግሬ | 26300 | 82225 | — | 100 | 231 | 207936 |
| 7 | አሩሲ | 13872 | 17826 | — | — | 20 | 27066 |
| 8 | ኢሉባቦር | 5397 | 28018 | — | — | 10 | 7470 |
| 9 | ከፋ | 29868 | 57347 | — | — | — | 72937 |
| 10 | ወለጋ | 28062 | 72128 | 1449 | 843 | 742 | 189935 |
| 11 | ወሎ | — | 56534 | 100 | — | — | 66505 |
| 12 | ገሙጎፋ | — | 16800 | — | — | 30 | 71000 |
| 13 | ጎጃም | 2226 | 3713 | — | 200 | — | 30955 |
| | ጠቅላላ ድምር | 224028 | 965806 | 32449 | 5309 | 1518 | 982085 |



በ1967 እና በ1968 ዓ.ም ዘማቾች ባሉባቸው ጣቢያዎችና አቅራቢያ የአካባቢውን ሕዝብ አስተባብረው በተገኘው
መዋጮና ዕቅድ ከሕዝቡ ጋር የሠሩአቸው በክፍለ ሀገር

| ተ.ቁ. | በክፍለ ሀገር /በፊደል ቅደም ተከተል | አነስተኛ መዋፊያዎች | አነስተኛ መታጠቢያዎች | አነስተኛ ሥላገበ መጠበቢያዎች | የእግረኛ መሸጋገሪያዎች | አነስተኛ መገበፊያዎች | የገጠር መጋቢ መንገዶች | መጠነኛ የውኃ ጉድጓዶችና አላዎች | የሽንት ቤቶች | መጠነኛ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች | የተጠረጉ ኩሬዎችና ምንጮች | የተከከሉ የገበያ ቦታዎችና አደባባዮች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 12 | 1 | 114 | 12 | — | 16 | 89 | 368 | 62 | 62 | 35 |
| 2 | ሲዳሞ | 93 | 14 | 325+ | 229 | 32 | 66 | 22 | 1354 | 106 | 160 | 3 |
| 3 | ሸዋ | 39 | 8 | 319 | 1079 | 14 | 120 | 341 | 535 | 353 | 482 | 96 |
| 4 | በጌምድር | 6 | 7 | 2 | 5 | — | 2 | 23 | 32 | 55 | 17 | 103 |
| 5 | ባሌ | 8 | 4 | 67 | 21 | — | 7 | 13 | 73 | 39 | 10 | 7 |
| 6 | ትግሬ | 18 | 11 | 66 | 32 | 3 | 72 | 197 | 176 | 176 | 135 | 4 |
| 7 | አሩሲ | 55 | — | 58 | 114 | 1 | 56 | 65 | 30 | 85 | 77 | 70 |
| 8 | ኢሉባቦር | 15 | 11 | — | 54 | — | 8 | — | 30 | 14 | 136 | 11 |
| 9 | ከፋ | 170 | 17 | 173 | 138 | — | 14 | 28 | 174 | 173 | 482 | 28 |
| 10 | ወለጋ | 17 | 14 | 264 | 344 | 27 | 148 | 82 | 179 | 228 | 567 | 38 |
| 11 | ወሎ | — | 8 | — | — | — | 2 | — | — | 10 | 13 | 17 |
| 12 | ገሙጎፋ | 97 | 69 | 4 | 71 | 10 | 18 | 109 | 569 | 247 | 30 | — |
| 13 | ጎጃም | 35 | 8 | 1 | 18 | — | 15 | 32 | 2451 | 904 | 98 | 2 |
| | ጠቅላላ ድምር | 565 | 168 | 1333+ | 2117 | 87 | 544 | 1001 | 5981 | 2452 | 2269 | 414 |

እንግዲህ ባጠቃላይ አነጋገር ዘማቾች ባገሩ አሉ ትግሉ ውስጥ ከፍተኛ ተግባር ፈጽመዋል:: ገበሬውን በማንቃት በማደራጀት ትጥቅ እንዲጠየቅ በማነሳሳት ባጠቃላይ አነጋገር ለአብዮታዊው ትግል መሠረት በመጣል ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል:: ይህም ትግላቸው ከፍተኛ ታታሪነትና ብርታት ይጠይቅ ነበር:: ከመካከላቸውም አንዳንዶቹ ለትግሉ መስዋዕት ሆነዋል::

ዘመቻውም መደገፍ የነበረበት /ያለበትም/ ለዚሁ ነው:: ስለሆነም፣ ገና ዘመቻው እንደተጀመረ ዘመቻውን ለማስቀረት የተደረገው ሙከራ፣ ወይ ከፀረ አብዮተኞች ወይ ከተሳሳቱ ተራማጆች የመጣ ነው ቢባልም፣ በተለይ ከመሬት አዋጁ ወዲህ ዘመቻውን ለማቋረጥ የተደረገው ጥሪ ፍጹም ፀረ ህዝብ ነበር:: ይህንንም ጥሪ የተከተሉት ወይንም የነቁ አድሃሪዎቹ፣ ስለዚያም ስለመደብ ትግል ምንም ያልተረዱ ግለሰቦች ናቸው:: ስለዚህም እውነት ከመካከላቸው ለህዝብ የቆሙ ካሉ፣ ስህተታቸውን በአብዮታዊ ቀናነት አምነው፣ ለትክክለኛው የትግል ፈለግ መቆማቸውን በተግባር ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል::

ዘመቻውና የልዩ ልዩ ጋዜጦችና ድርጅቶች አቋም

ይህንን ነጥብ በዝርዝር ከማየታችን በፊት አንድ ለመስማማት የሚያስፈልግ ነጥብ አለ:: ማንኛውም ጋዜጣ ወይንም ድርጅት ያገሩን መደብ ወይንም የተወሰኑ መደቦችን ጥቅም ያንጸባርቃል:: ማንኛውም መደብ ባንድ ባንድ አብዮታዊ ትግል ወቅት የተወሰነ ዓላማ አለው:: በድርጅትም አማካይነት የሚያደርገው ትግል ይህን ዓላማውን በሥራ ለመተርጎም ነው:: በሌላ አነጋገር አንድ ድርጅት ለየትኛው መደብ እንደቆመ የሚያሳየው ራሱ እንደሚለው ብቻ ሳይሆን በተግባር የየትኛውን መደብ ጥቅም እንደሚያገለግል ሲታይ ነው:: በኢትዮጵያም የሚገኙ ነፃ ጋዜጦችና ድርጅቶች ከዚህ ሳይንሳዊ ህግ የሚወጡበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም:: ስለዚህም በኢትዮጵያ ያሉም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ ድርጅቶች በዘመቻው ላይ የወሰዱት አቋም የሚወክሉትን መደብ ጥቅም የሚያንፀባርቁትን ያህል የያንዳንዱ ድርጅት አቋም የድርጅቱን ጠባይ ይጠቁማል::

“ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ህብረት” የተባለው የነአስፋወሰን በረት ባወጣው መግለጫ ላይ ዘመቻውን በመቃወም ግልጽ የሆነ አቋም ወስዷል:: ለዚህ የሰጠው ምክንያት “ የኢትዮጵያን ወጣቶች ከትምህርት ነጥሏቸው ” የሚል ተረት ነው::

በእውነቱ ይህ ምክንያት የአዞ እንባ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ምርመራን አይጠይቅም:: በዘመኑ ሃይለስላሴ የኢትዮጵያ ወጣቶች ምን ያህል የትምህርት እድል እንደተነፈጋቸው ማስታወሱ ይበቃል:: ይልቁስ አስፋወሰን ዘመቻውን የተቃወመበትን ትክክለኛ ምክንያት የትኛው ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በንቅክር ምናልባት ዘመቻውን የተቃወሙትን ‘ተራማጆች’ ያመራረቸው ይሆናል::

“ ኢዲዩ ” ዘመቻውን የተቃወመው “ ተማሪው ከከተማው ከተነሳ የፀረ አብዮት ሃይሎች በሥልጣን ላይ ይደላደላሉ” ከሚል ፍራቻ አይደለም:: ቢሆንማ ዘመቻውን ደስ ብሎት በተቀበለ ነበር:: “ኢዲዩ” ዘመቻውን የተቃወመው ከፍ ብለን እንደገለጽነው፣ “ገፈሳ ደር የሌለው ገበሬና ተማሪ” ሲገናኝ ደግ አይደለም



ከሚለው የባላባት ስጋት ተነስቶ ነው:: ምክንያቱም ተማሪው ከገበሬው ከተዋሃደ ባላባታዊው የመሬት ስሪት አደጋ ላይ እንደሚወድቅ “ኢዲዩ” አሳምሮ ያውቃል:: በነገራችን ላይ ዘማቾች ያከናወኑትን ሥራ ስናይ፣ ይህ የነአስፋወሰን ስጋት ምን ያህል ትክክለኛ ስጋት እንደነበር እንረዳለን:: ከዚህም አልፎ የተማሪውና የገበሬው መዋሃድ አብዮቱን ማራመድ ብቻ ሳይሆን፣ የፀረ አብዮት ቀለበቱ እንዳይሳካ፣ ይህን ቀለበት ለመቋቋም የማይናቅ ሃይል በገጠር እንደሚፈጠር እነ አስፋወሰን በሚገባ ተረድተው ዘመቻውን አምረው ተቃውመዋል::

ባጭሩ ባላባቶች ዘመቻውን የተቃወሙት ከመደብ ጥቅማቸው ተነስተው እንደማይበጃቸው ተገንዝበው ነው::

የዘመቻው ተቃዋሚ ክፍል በነ ‘ኢዲዩ’ አይወሰንም:: ‘ኢሀአፓ’ ‘አብዮታዊ ወጣት’ ወዘተ የተባሉት ድርጅቶች ይቃወሙታል:: ለተቃውሞአቸው የሰጡትን ሰበብ ከፍ ብለን ስህተተኛ እንደነበረና በተለይ ከመሬት አዋጁ ወዲህ ፍጹም ፀረ ህዝብ ይዘት እንደነበረው አሳይተናል::

“ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት”፣ ካልተቋቋመ ለተዘመቱ ፣ ዘመቻው የደርግን ፋሽዝም በገጠር ለማስፋፋት ነው ወዘተ “መባሰሉት ማስፈራሪያቸው ዛሬ ማንም ሃቀኛ ታጋይ አያታልሉም አያስደነግጡም:: እንደውነቱ ከሆነ ዛሬ ‘ኢሀአፓ’ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ የመደብ አሰላለፍ የያዘውን ቦታ በተረዳነው፣ በአድሃሪዎች የኢኮኖሚ አሻጥርና የፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ያለው ከፍተኛ ተባባሪ ካየን በዘመቻው ላይ በወሰደው ፀረ ህዝብ አቋም ባልተደነቅን ነበር:: ይሁንና በተራማጅ መስለ ያሉት እየተበቁ ብዙ ፀኑ ተራማጆችን አሳስተዋል፣ ‘ኢሀአፓ’ ዘመቻውን የተቃወመው አብዮቱን ለማራመድ ሳይሆን ዘመቻው በሚያራምደው ሥር ነቀል አብዮታዊ እንቅስቃሴ የመደብ ጥቅሙን ስለሚፃረርበት መሆኑን አሁንም በድጋሚ መግለጽ ያስፈልጋል:: ሃቀኛ ተራማጆችም ይህንን እውነት በሚገባ መረዳት ይኖርባቸዋል::

በበኩላችን ‘ኢሀአፓ’ በወሰደው ፀረ ህዝብ አቋም ባንደነቅም ሳንቀረደው አናልፍም፣ በተራማጆች ዘንድ ማንነቱን ከማጋለጥ አንቆጠብም:: የዚህን የከሃዲ ምሁሩን በረት ከሰፊው ህዝብ ጎን ሆነን እንታገላለን:: ተሸናፊነቱንም የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል እያረጋገጠ እንደመጣ ሁሉ፣ ለወደፊቱም ይህ አዝማሚያ እያየለ እንደሚቀጥል አንጠራጠርም::

በሃገር ቤት ያሉ ተራማጅ ድርጅቶች በዘመቻው ላይ የወሰዱትን ስሌቶች፣ አቋሞች ተቃውመዋቸዋል፣ ለወደፊትም ይደግፏቸዋል:: ‘ኢዲዩ፣ ኢሀአፓ’ ውስጥ አዋቂና የውጭ ሰው ሆነው ዘመቻውን ከመጀመሪያው አስከመጨረሻው ለማደናቀፍ ቢጣጣሩ፣ የመንግሥቱ ቢሮክራሲ፣ ፖሊስና የደርጉ ቀኝ ክንፍ ቢተባበሯቸው ተራማጆች እጃቸውን አጥፈው አልተቀመጡም:: እነ መኢሶን፣ ሬቮሉሽን፣ የአብዮት ፋና፣ ታጋይ ኢትዮጵያዊት ወዘተ ዘመቻው ሲታወጅ ከዚያም የመሬት አዋጅ ሲወጣ “ ተማሪና ምሁር ከገበሬውና ሰራተኛው ተዋሃድ ” የሚለውን መሪ ቃል በሥራ ለመተርጎም ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል::

በዚህ ትግላቸው ባላባቱን፣ ቢሮክራሲውንም ሆነ የደርጉን ቀኝ ክንፍ እንዲሁም ‘ኢሀአፓ’ን የመሳሰሉትን አድር ባይ ፀረ ህዝብ ድርጅቶች ታግለዋል:: ለዘመቻው ትክክለኛ አቅጣጫ በመስጠት፣ ዘማቾች የመሬቱን አዋጅ በሥራ ለመተርጎም እንዲጥሩ ፣ ገበሬው ትጥቅ እንዲጠይቅ እንዲያነሳሱት ከፍተኛ ቅስቀሳ አካ

ሃይ ዋስ::

እነዚሁ ተራማጅ ድርጅቶችና ተራማጅ ዜጎቻቸው ያካሄዱት ትግል ያስገኘው ውጤት በምናይበት ጊዜ፣ ምን ያህል አብዮታዊው እንቅስቃሴ መሰረት እንደጣሉና ምን ያህል አድሃሪዎቻቸውና አድርባዮች እንደተጋለጡ በምንገነዘበበት ጊዜ ተራማጆች አሁንም የያዙትን የትግል ፋና በይበልጥ መቀጠልና ወደፊት መራመድ እንዳለባቸው እንረዳለን:: ለማጠቃለል ዓመታትም ይሁን የትግል ፋና የያለው ሰፊው ጭቁን ህዝብ በገዢነት ተነስቶ የራሱን ህዝባዊ መንግሥት ፲ በወዝ አደሩ በሚመራ በነቃ በተደራጀና በታጠቀ ትግል ሲመሰረት ይታያል::

ማጠቃለያ

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ግልጽ የሆነ አቅጣጫ በያዘበት ወቅት፣ የሰፊው ጭቁን ህዝብ ወገንና ጠላት በሰፊው በግልጽ እየለዩ በሄደበት ሰዓት ተራማጅ ወጣቶች ሚናቸውን በትክክል መወሰን አለባቸው::

የሰፊው ህዝብ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የያዘውን ግልጽ የሆነ ፀረ ባላባት፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም አቅጣጫ ወደፊት ለማራመድ በፊናቸው ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማበርከት አለባቸው::

በዚሁ መጠን የሚፈለጉትን የሕዝብ መንግሥት በምርጫ እንደማያገኙት ተረድተው፣ ይህንን መንግሥት በምርጫ ወይም በመፈንቅለ መንግሥት ሳያሟሉ ው የሚሊገኙ በነሱ ሰፊ የሚገለገል አወናባጅ ፀረ ህዝብ ሃይል መሆኑን ተገንዝበው፣ በወዝ አደሩ ጋር ቴ የሚመራውን በፊ ፀረ ባላባትና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ግንባር ለማቋቋም የሚደረገውን ትግል ማፋፋም ይኖርባቸዋል:: ለሰፊው ህዝብ ነፃ መውጫ ከዚህ ሌላ ምንም መንገድ የለምና::

ተራማጅ ድርጅቶችና ተራማጅ ዜጎቻቸው በዚህ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል:: ለወደፊትም ካለፈው በላቀ መልክ መቀጠል አለባቸው:: ሰፊው ወጣ ትም በነሱ ፈለግ መሰለፍ ይኖርበታል:: ከዚህ በፊት በፀረ አብዮት የአናርኪስቶች ቅስቀሳ የተሳሳተ ሁሉ በህብረትን በአብዮታዊ ቀንነት አርሞ ለትክክለኛው የትግል አቅጣጫ መቆም ይኖርበታል:: በአኢተማ 16ኛ ጉባዔ በትክክል እንዳሰመረው "እነዚህ በታላቅ መስዋዕትነት የተገኙት አብዮታዊ ድሎች እንዲከበሩና ወደፊትም የገጠሬውንና የከተማው አብዮታዊ አንድነት ተጠብቆ እንዲገኝ ለማስቻል፣ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 16ኛ ጠቅላላ ጉባዔ የዚህ ዘመቻ መቀጠልን ይደግፋል:: ሆኖም ወደፊት ዘመቻው በሚከተለው መልክ መቀጠልና መደራጀት ይኖርበታል::

1. ዘመቻው በበጎ ፈቃደኛነት መመስረት አለበት
2. ዘማቾች በበለጠ ተግባራቸውን ለማጠናቀቅ እንዲችሉ የፖለቲካ ትምህርት እንዲሰጣቸው ያስፈልጋል::
3. የአድሃሪያንን አመጽ ለመከላከል እንዲችሉ እንደየቦታውና እንደሁኔታው የውትድርና ትምህርት እንዲሰጣቸው ያስፈልጋል
4. በሃገር አቀፍ ደረጃ እንዲደራጁና የራሳቸው ነፃ ጋዜጣ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል::"

---



በ16ኛው የአ/ኢ/ተ/ማ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ስለ ዘመቻው የተላለፈ ውሳኔ

---

.../...

ስለ ዘማቾች

ባገር ቤት የሚገኙት የኢትዮጵያ ወጣቶች በኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ውስጥ ታላቅ አብዮታዊ ሚና የተጫወቱ ናቸው:: በተለይ አሁን በመካሄድ ላይ ባለው አብዮት በመሳተፍ፣ ሰፊው ህዝብ እንዲነቃ፣ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ያሳዩት ከፍተኛ ትግል፣ በህዝባችን ትግል ታሪክ ውስጥ አኩሪና ታላቅ ቦታ ይይዛል::

ከሁለት ዓመት በፊት የታወጀው የዕድገት በህብረት ዘመቻ አማካኝነት የኢትዮጵያ ወጣቶች ምሁራን፣ ከሰፊው ህዝብ ጋር ተቀላቅሉ የሚለውን መፈክር ሥራ ላይ ለማዋል በገጠርም ሆነ በከተማ ተሠማሩ፤ በዚሁ አጋጣሚ ለአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መጠናከር ቁልፍ የሚሆኑና ሊናቁ የማይቻሉ አብዮታዊ ድሎችን ተቀዳጅተዋል:: ከነዚሁ ሁሉ ቶን ለመዘርዘር:-

ሀ/ መሬትን ለአራሹ ሥራ ላይ ለማዋል በተደረገው ትግል ገበሬውን በማንቃት፣ በማደራጀትና ትግሉን በመገፋት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገዋል፣

ለ/ ወደፊት ለሚቋቋመው የወዝአደሩና የገበሬው ኅብረት መሠረት የሆነውን የከተማውንና የገጠሩን አብዮታዊ አንድነት ፈጥረዋል::

እነዚህ በታላቅ መስዋዕትነት የተገኙት አብዮታዊ ድሎች እንዲከበሩና ወደፊትም የገጠሬውንና የከተማው አብዮታዊ አንድነት ተጠብቆ እንዲገኝ ለማስቻል፣ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 16ኛ ጠቅላላ ጉባዔ የዚህ ዘመቻ መቀጠልን ይደግፋል:: ሆኖም ዘመቻው ወደፊት በሚከተለው መልክ መቀጠልና መደራጀት ይኖርበታል::

1. ዘመቻው በበጎ ፈቃደኛነት መመሥረት አለበት
2. ዘማቾች በበለጠ ተግባራቸውን ለማጠናቀቅ እንዲችሉ የፖለቲካ ትምህርት እንዲሰጣቸው
3. የአድሃሪያንን አመጽ ለመከላከል እንዲችሉ እንደየቦታውና እንደሁኔታው የውትድርና ትምህርት እንዲሰጣቸው ያስፈልጋል
4. በሃገር አቀፍ ደረጃ እንዲደራጁና የራሳቸው ነፃ ጋዜጣ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል::

በአኢተማ 16ኛ ጉባዔ በተከፈተበት ወቅት ፲ በገበሬው ጎን ተሰልፈው ህይወታቸውን የሰጡ ዘማቾች ስም በክብርዕት ከተነበበ በኋላ ጉባዔው ለነዚህን ሰማዕታቶች ለዘወስኑ ደቂቃዎች በፀጥታ በማስታወስ ሀዘኑን ገልጿል:: ማህበራችን በድጋሚ ለነዚህ ህይወታቸውን ለአብዮቱ ለሰጡ ዘማች ጓዶቻችን ሀዘኑን ይገልጻል::

ለዚህ ለደረሰባቸው አሰቃቂ አደጋ ተጠያቂዎቹ፣ ለህይወታቸው በቂ ጥበቃ ባያደርጉላቸው ለፀረ አብዮት ሃይል ያጋለጧቸውና ራሱም ቀጥቶ ቅጣት የፈጸመባቸው ፀረ ዲሞክራሲ የደርግ አገዛዝ፣ የፖሊስ ሠራዊት፣ እንዲሁም በተራማጅና በዘማቾች መሃል ሰርጎ የገባው 'የዲሞክራሲያ'/ኢፒአር ፒ/ ድግሬ ቡድንን የማጠሰው ከፋፋይ ,የገበሬ ከበርቴ ፒርሚካቲር ቡድን፣ ከዚያም 'ኢ.ዲ.ህ.'ና በአገር ውስጥ የሚገኙ ፊውዳሊስቶችና የቢሮ ከበርቴዎች መሆናቸውን ያረጋግጣል::

# ተማሪና ምሁር
# ከሠራተኛውና ከገበሬው
# ተዋሀድ፣ ከነርሱ ተማር
# መልሰህም
# አስተምሪቸው